# <u>ስንዝሮ ፖለቲከኞች</u>

ከበልጅግ አሊ

-፩-

ከአንዱ ወደ አንዱ እየዘለልኩ ድረ ገጾችን ሳላዳርስ አልውልም። ድረ ገጾች ሕዝብን ለማስተማር፣ በሃገራችን የተከለከለውን ነጻ ፕረስ ለማስቀጠል የሚያደርጉትን ጥረት አደንቃለሁ። ድረ ገጾቹ ድክመት የላቸውም ማለት አይደለም። ልብ ብሎ ለተከታተላቸው ብዙ የሚገርም ክስተትም ይስተዋልባቸዋል። በፈቃደኝነትና በትርፍ ሰዓት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከመሆኑ አንጻር ይህንን አላደረጉም ብሎ መውቀሱ ግን ይከብዳል። ቢሆንም ግን የተዛባና ህዝብን ለእርስ በርስ ግጭት የሚገፋፉትን  አቁሙ ልንላቸዉ የሚገባን መሆኑ በፍጹም አጠያያቂ አይሆንም።

ይህንን ያስባለኝ  አንድ  በጽሞና የታዘብኩት ጉዳይ በመኖሩ  ነው። በሕፃንነታችሁ የስንዝሮን ታሪክ አንብባችኋል ብዬ እገምታለሁ። ሰኞ ተረገዝኩ፣ ማክሰኞ ተወለድኩ፣ ረቡዕ ክርስትና ተነሳሁ፣ ሐሙስ ሚስት አገባሁ፣ አርብ ሞትኩ የሚል ዓይነት ታሪክ። የዚህ ዓይነቱ  ጉደኛ ታሪክ ያላቸው  ፖለቲከኞች ያው እንደተለመደው በአሁኑ ወቅትም በብዛት  ብቅ ብቅ  በማለት ላይ ናቸዉ።

በፀረ ወያኔ ትግል ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦች ሳይታሰቡ ጣሪያ ነክተዉ ሁሉን አወቅን ሲሉ መመልከት ከጀመርን ከራረምን። እነዚሁ ግለሰቦች ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲክዱ ፍጥነታቸው ከብርሃን  ጋር ይወዳደራል። ልደቱ (ክህደቱ ተብሎ ከመንደባለሉ በፊት ) በአንድ ጊዜ  ላይ የታጋይ ቁንጮ ተደርጎ ከተወደሰበት ጣሪያ እንዲወጣ የተደረገው በወያኔ መሆኑን የተገነዘብነው በቅርቡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወሳኝ በሆነ ወቅት  ላይ ከድቶ ከወያኔ ጎን ሲቆም ነው። ልደቱን ገና ከአጀማመሩ እረ ረጋ እንበል ያሉ ተሰድበውም ነበር። “ወጣቱ እንዳይታገል ነው“ ብለው ያሙም ነበሩ። ግን ለልደቱም ይሁን ለትግሉ ያ የተጋጋለ አንቱታ ጠቃሚ አልነበረም። የልደቱን ልብ ሲያሳብጥ ትግሉን ደግሞ በጣም ጎድቶታል። የሰቀልነውን ማውረድ አቅቶን በሥማችን የማንፈልገውን ከወያኔ ጋር ሲደራደርብን ሰነባበተ። ከልደቱ ጋር በቀጥታ ከሚያያዙት ነሁለላዎች ሁሉ  የሚገርመኝና የማልዘነጋዉ  የአንጋፋው የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት መሪዎች ድርጅታቸውን ለልደቱ  ማስረከባቸው ነው። ይህ አንዱ ከስንዝሮ ታሪክ የሚመሳሰል ትርክት ነው።

ምርጫ በደረሰ ቁጥር የሚነሱ ስንዝሮዎች ደግሞ በቁጥር ብዙ፣ በግብር አስቂኞች ናቸው።  ሰኞ ዕለት ፖለቲካ ይጀምራሉ፣ ማክሰኞ ኢንተርቪው ይደረጋሉ፣ ረቡዕ የፖለቲካ ተንታኝ፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ  ይሆናሉ፣ ሐሙስ ዘረኛ ይሆናሉ፣ አርብ ላይ ወደ እዉነተኛዉ ማንነታቸዉ ተመልሰው ከወያኔ የዘፈን መድረክ ላይ እመር ብለዉ ይወጡና በሎ - በሎ በሚል ዜማ ለመደንከር ነጠላቸዉን ያሸርጣሉ።  ምን አልባት ከእነርሱ የሚጠበቀው እስከሚታወቁ ድረስ አንዱን ድርጅት ደግፎ ሌላውን መስደብ ነው። ከዚያ ሁሉም  ነገር አልጋ ባልጋ ይሆናላቸዋል።

ባለፈው ምርጫም የሆነው እንዲሁ ነው። ብዙ ስንዝሮ  ፖለቲከኞች  ራሳቸዉን ወደ ትግሉ አስገብተው ከፖለቲካው ማዕበል ጋር ሲዋዥቁ ቆይተዋል። ያ ደግሞ ለወያኔ በጣም ጠቅሞታል። ምርጫ ይገባ፣ አይገባ ላይ በየቦታው ቃለ መጠይቅ ሲሰጡ የነበሩት አዳዲሶቹ የፖለቲካ ስንዝሮዎች  ነበሩ።  የቀድሞዎቹን ድርጅቶችና መሪዎች በመውቀስ ይነሱና የእነርሱ ሃሳብ ግን  ትክክለኛዉና  ዋነኛው መንገድ መሆኑን በተደጋገመ መሓላ በማስረገጥ ሲያወናብዱ ከርመው ነበር።  ምርጫው ካለፈ በኋላ  ግና ተልዕኳቸው ተፈፀመ  መሰል ይሔዉ እስከዛሬ ድራሻቸውም አልተገኘም። እነዚህ ስንዝሮ ፖለቲከኞች  አድማጫቸዉን ለማወናበድ ይዘው የሚመጡትን ጣፋጭ የቃላት ድርደራ ወደጎን ትተን ትንሽ ፋቅ ብናደርጋቸው እውነተኛ የሻዕብያ ቅጥረኝነታቸው ፣ ቀንዳም  ዘረኝነታቸው፣ በተለይም ፀረ አማአራነታቸው ብቅ ይላል።

ሰሞኑን በግርምት ያስተዋልኩት የ ታሪኬ በአጭሩ ዐይነት ፖለቲከኛ ደግሞ  በአሁኑ ወቅት በየቦታው የሚገኝ አንድ ወጣት ነው።  ጃዋር ሲራጅ መሐመድ ይባላል። መቼ ተረግዞ ምኔ እንደተወለደ አትጠይቁኝ።  ከዉዳሴዉ ጣሪያ ላይ ወጥቶ  ያነበነበዉን ቃለመጠይቁን ያነበብኩት የአማርኛና የእግሊዘኛ ስም ካለው ጋዜጣ ነው፡፡ "የአውራምባ ታይምስ"። ይህንን ጉድ ስላስነበበን አዉራምባ ታይምስን  ልናመሰግነው ይገባል።   ባለፈው ሰኞ የፖለቲካ ሕይወቱን የጀመረውን  ይህን ወጣት ስንዝሮ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ የፖለቲካ ተንታኝ የሚል ማዕረግ ሸልመዉት  ራዲዮውና ድረ ገጹ፣ ሰው ሰለተሰበሰበ ትልቅ ስራ የሰሩ የሚመስቸው ፓልቶኮች ሳይቀሩ ሲቀባበሉት ከርመዋል።  ወጣቱን በግሌ አላውቀውም ግን ደግሞ በየቦታው ሲረገድለት መቆየቱ ሳይገርመኝ አልቀረም። ከላይ በጠቀስኩት ጋዜጣ ላይ ካነበብኩት ቃለመጠይቁ ግን ግለሰቡ ማን እንደሆነና ለምን እንደሚታገል ወለል ብሎ  ታይቶኛል።

ግለሰቡ ስለኢትዮጵያ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለመበታተን የሚደረገውን ትግል ደጋፊ መሆኑን ሳይደብቅ ተናግሯል። ይህ ግለሰብ ወደ ትግሉ ብቅ ብሎ ታዋቂነት ማግኘትን የጀመረው አል ጀዚራ በሚባለው የአረቦች ቴሌቪዥን

ላይ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ነው። በ 1995 ዓ.ም የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት ስኮላርሺፕ አግኝቶ ወደ ሲንጋፖር የሄደው ወጣት ገና ሕፃን እያለ ነበር ከኦነግ የተገናኘው። መገናኘት ብቻ ሳይሆን መደገፍ የጀመረው።

ኦነግ በሕዝብ ልብ ውስጥ ያለ ድርጅት ነው በማለት በድፍረት የሚነግረን ወጣት ከወያኔ ጋር ሥልጣን ላይ ወጥቶ የነበረው ኦነግ በፀረ አማራነት አርባ ጉጉና አሰሳ ላይ የፈፀመውን ድርጊት ሊያነሳው አይፈልግም። ሊወቅስ የሚፈልገው በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ ኦሮሞዎችን ነው። የዚህ ስንዝሮ ፖለቲከኛ ፀረ አማራ አቋም ጎልቶ የሚታየው ኦነግን ሲያደንቅና የአማራውን ጭፍጨፋ ሲዘነጋ ነዉ። ይህ ነው እንግዲህ የአዲሱ የፖለቲካ ስንዝሮ የፖለቲካ ተንታኝነት፡፡ ይብስ ብሎ የኦነግን ዓላማ ለማስፈፀም መደረግ አለባቸው የሚለውን ሊዘረዝር ሞክሮል። የኦነግ አላማ ለእኔ እንደሚገባኝ ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። ወጣቱ ለዚህ እኩይ ዓላማው ኢትዮጵያዊያን ይረዱኛል ብሎ ማሰቡ የሚገርም ነው። ይህንን የመሰለዉን ደፋር ነዉ መሰል ያራዳ ልጆች “ፈጣጣ“ የሚሉት። ፈጣጣነት ከተወሳ አይቀር ወጣቱ ተንታኝ እግረመንገዱን ያነሳዉን አንድ ሌላ ቀልድ ላመልከታችሁ። የወያኔዉ የኦሮሞ ክንፍ - ያባዱላዉ ኦሕዴድ - ታታሪ ብልህና ሀገር ወዳድ ግለሰቦችን ያቀፈ ነዉ ይልልናል። ከዚህ የባሰ የምን ቀልድ ይመጣል ???? ምነዉ ተንታኙ የሚያወድሰውን የሆዳሞች መጠራቀሚያ ጠፍጥፎ የፈጠረዉ የወያኔ መሪ ይህንን ቀልድ በሰማና በሳቅ ፈንድቶ በሞተ። ..... ጆሮን ለምን አታድግም ??? ቢሉት ... ይህንን ሁሉ ጉድ እየሰማሁ በዬት ?? ብሎ መለሰ ነዉ የሚለዉ ተረቱ??? ... ምንኛ ድንቅ ብሏል ጃል????

ይህ ዘረኛ ፖለቲከኛ የአረብ ቴሌቪዥን ሳይቀር ሊጋበዘው የበቃው በዚሁ በፀረ ኢትዮጵያ አቋሙ ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ይኖርብናል። ለምን አልጀዚራ ሌሎች ታዋቂ የፖለቲካ መሪዎችን ሳይጋብዝ ስንዝሮውን ፖለቲከኛውን ጋበዘ? የሚለው ጥያቄ በግሌ አሳስቦኛል። ሌሎቻችሁም እንደኔ ይሰማችሁ ይሆናል።

በዚህ ጽሁፍ ለኢትዮጵያዊያን ድረ ገጾች፣ ፓልቶኮች፣ ጋዜጦች፣ ራዲዮና ቴሌቪዥኖች በኢትዮጵያን ገንዘብ በሚንቀሳቀሱ ክፍሎች የሕዝብን ገንዘብ ለፀረ ኢትዮጵያ ቅስቀሳ ሊያውሉት አይገባም እላለሁ። ዛሬ ኦነግን፣ ኦሕዴድን ማቆላመጽ የጀመረው ይህ ግለሰብ ዘረኛ አቋሙን ትቶ ለሁሉም ዘሮች በእኩልነት የተመሰረተች ኢትዮጵያን ለመመስረት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ ከፈለገ በመጀመሪያ በተወሰኑ ዘሮች ላይ ያለውን ጥላቻ ሊፍቅ ይገባል። አማራው ሲጨፈጨፍ እኔም አማራ ነኝ፣ ኦሮሞው ሲበደል እኔም ኦሮሞ ነኝ፣ ትግሬውም ሲበደል እኔም ትግሬ ነኝ ብሎ የግሌ ዘሬ ነው ብሎ ከሚያምነው ዘር ባሻገር ለኢትዮጵያዊነት ሲታገል ብቻ ነው በኢትዮጵያውያን በተሰበሰበ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ መዋቅሮችን ሊጠቀም መፈቀድ ያለበት። ከዚያም ባሻገር የኢትዮጵያ ጠላት የሆኑ ሜዲያዎች ስላስተዋወቁት ብቻ ያንን ተቀብለን እኛም አብረን ልናረበርብ አይገባም። ይህንን ስንዝሮ ፖለቲከኛ ጣሪያ ላይ ያለቦታዉ ሰቅለን በሁዋላ ማዉረዱ እንዳይቸግረን ልንጠነቀቅ ይገባል። መድረከም እየሰጠን መልሶ እኛኑ እንዲዋጋን ማድረግ የለብንም ።

ስለ ኢትዮጵያ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !